

ቅዱስ ዮሐንስ

ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ

ቅዱስ ማትያስ

‹‹ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ፤ የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል›› (መዝ. ፻፲፩÷፮)

ቅዱስ ዮሐንስ

‹‹ የእግዚአንሔር ጸጋ ››

‹‹ ፍስሐ ወሐሴት ››



መስከረም ፭ ቀን በገሊላ አውራጃ በ ቤተሳይዳ **ከዘብዴዎስና ከማርያም ባውፍልያ** ተወልደ።



የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙር ነበር **/ዮሐ.፩፡፴፮-፵/**።



በቅፍርናሆም ከተማ በገሊላ አጠገብ ተጠራ /ማቴ.፬፡፳፩/።

ጌታችን ሲጠራው የ፷፭ ዓመት ወጣት እንደ ነበረም ሄሬኔዎስ የተባለደቀ መዝሙሩ ጽፏል።

ቅድስት ማርያም እሞሙ ለደቂቀ ዘብዴዎስ

የዮሐንስ ወንጌል ፩
35፤ በነገው ደግሞ ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱም ሁለት ቆመው ነበር፥
36፤ ኢየሱስም ሲሄድ ተመልከቶ፦ እነሆ የእግዚአብሔር በግ፡ አለ።
37፤ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሲናገር ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት።
38፤ ኢየሱስም ዘወር ብሎ ሲከተሉትም አይቶ፦ **ምን ትፈልጋላችሁ**? አላቸው። እነርሱም፦ **ረቢ፥ ወዴት ትኖራለህ?** አሉት፤ ትርጓሜው፡ መምህር ሆይ፡ ማለት ነው።
39፤ **መጥታችሁ እዩ**፡ አላቸው። መጥተው የሚኖርበትን አዩ፥ በዚያም ቀን በእርሱ ዘንድ ዋሉ፤ አሥር ሰዓት ያህል ነበረ።
40፤ ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበረ።

የማቴዎስ ወንጌል 4
21፤ ከዚያም እልፍ ብሎ ሌሎችን ሁለት ወንድማማች የዘብዴዎስን ልጅ **ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በታንኳ መረባቸውን ሲያበጁ አየ፤ ጠራቸውም።**
22፤ እነርሱም ወዲያው ታንኳይቱንና አባታቸውን ትተው ተከተሉት።

የቅዱስ ዮሐንስ ስሞች

- **ወልደ ነጐድጓድ** /ማር.፫፡፲፯/
- **ታዖሎጐስ**-ነባቤ መለኰት
- **አቡቀለምሲስ**-ረአየኁቡአቸ̈ ~ ባለ ራዕይ
- **ቁጹረ ገጽ**- ፊቱ በሐዘን የተቋጠረ
- **የመሥጢር ልጅ**
  - ጌታችን ግርማ መንግሥቱን ሲገልጥ /ማቴ.፲፯፡፩/፣
  - የኢያኢሮስን ልጅ ሲያነሣ /ማር.፭፡፴፯/፣
  - በጌቴሴማኒ የአታክልት ቦታ ሲጸልይ/ማቴ.፳፮፡፴፯/፣
  - ስለ ኢየሩሳሌም መጥፋት ትንቢት ሲናገር/ማር.፲፫፡3/
- ቅዱስ ጳውሎስ **አዕማደ ቤተ ክርስቲያን** ብሎ ከሚጠራቸው ሐዋርያት አንዱ ዮሐንስ ነው /ገላ.፪፡፱/
- **ፍቁረ እግዚእ** - የጌታ ወዳጅ /ዮሐ.፲፫፡፳፫/

የቅዱስ ዮሐንስ ሰብክት

- በኢየሩሳሌምና በአከባቢው ጀመረ ወደ አንጾክያ ሄዶም አስተምሮል

  ሐምሌ ፭ የሚነበበው መጽሐፈ ስንክሳር

- መጨረሻ አከባቢ ያስተማረው በእስያ ሀገር ሲኾን ዋና መንበሩም **ኤፌሶን**

  ጥር ፬ የሚነበበው መጽሐፈ ስንክሳር

- ፍጥሞ ደሴት

  በኤፌሶን በሚያስተምርበት ጊዜ ከኔሮን ቄሣር ቀጥሎ በሮም የነገሠው ድምጥያኖስ (፹፮-፺፮ ዓ.ም) የራሱን ምስል አሠርቶ እንዲሰገድለት ወደ ኤፌሶን ላከ

  - ራዕዩን ያየውና የጻፈውም በዚያ ቦታ ነው

- ድምጥያኖስከ ተገደለ በኋላ ከግዞቱ ተመልሶ ሦስቱን መልእክታቱና ወንጌሉን ጻፈ

የቅዱስ ዮሐንስ መጻሕፍት

ወንጌል



- **ዓላማ**

  “ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።” (ዮሐ 20፥30-31)

- **፳፬ ምዕራፍ**

መልእክታት



1ኛ የዮሐንስ መልእክት

- **ዓላማ**
  - ክርስቲያኖች ከዘላለማዊ አምላክ ጋር አስደሳች ኅብረት ሊያደርጉ እንደሚችሉ ማስገንዘብ (1ኛ ዮሐ 1፡4)
  - ክርስቲያኖች **የተቀደሰ ሕይወት መኖር እንዳለባቸው** ለማብራራት (1ኛ ዮሐ 2፡1)
  - አማኞች **በፍቅራቸው ተለይተው እንዲታወቁ** ለማበረታታት (1ኛ ዮሐ 2፡7-8)
  - አማኞች በክርስቶስ ባመኑበት ወቅት እግዚአብሔር **የዘላለምን ሕይወት ስጦታ** እንደሰጣቸው ለማረጋገጥ (1ኛ ዮሐ. 5፡13)
  - አማኞችን በማወክ ላይ ያለውን **የሐሰተኛ አስተማሪዎች ትምህርት ለማፍረስ** (1ኛ ዮሐ 2፡19)

- **፭ ምዕራፍ**

2ኛ የዮሐንስ መልእክት

- **፩ ምዕራፍ**

የቅዱስ ዮሐንስ መጻሕፍት

መልእክታት



3ኛ የዮሐንስ መልእክት

- **ዓላማ**
  - የላካቸውን አስተማሪዎች ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሳይቀበሏቸው **ጋይዮስ** ግን ስለተቀበላቸው ላከናወነው መልካም ተግባር ምሥጋና ለማቅረብ
  - ክርስቲያኖች **ዲዮጥራጢስ** ከተባለ የቤተ ክርስቲያን መሪ ተግባራት እንዲጠነቀቁ ለማሳሰብ
  - አማኞች እውነትን እንዲያውቁና በዚሁ እውነት ላይ ጸንተው እንዲቆሙ

- **፩ ምዕራፍ**

ራዕይ




- **ዓላማ**
  - 7ቱ አብያተ ክርስቲያናት ራሳቸውን እግዚአብሔር በሚያያቸው መንገድ እንዲገመግሙ ለማበረታታት
  - አማኞች በስደት ጊዜ በታማኝነት ጸንተው እንዲቆሙ ለማበረታታት
  - ለአማኞች በስተጀርባ ያለውን የዓለም ታሪክ ለማሳየት

- **፳፪ ምዕራፍ**

ፍፃሜ

በዮሐ. ፳፩፡፳-፳፫ ላይ የተጻፈውን መነሻ በማድረግ
“ዮሐንስ ሞትን አልቀመሰም”

- **ጥር ፭ የተሰወረበት ቀን ነው**



#2

ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ

“አዕቆጼ ሰኮና- ተረከዝ ያዥ”



ከዘብዴዎስና **ከማርያም ባውፍልያ** ተወልደ



አሳ አጥማጅ ነበር



በቅፍርናሆም ከተማ በገሊላ አጠገብ ተጠራ
/ማቴ.፬፡፳፩/::

የማቴዎስ ወንጌል 4
21፤ ከዚያም እልፍ ብሎ ሌሎችን ሁለት ወንድማማች የዘብዴዎስን ልጅ **ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በታንኳ መረባቸውን ሲያበጁ አየ፤ ጠራቸውም።**
22፤ እነርሱም ወዲያው ታንኳይቱንና አባታቸውን ትተው ተከተሉት።

የቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ሰብከት

- ኢየሩሳሌም
- በሰማዕትነት ከማለፉ በፊት በ ስፔን

ፍፃሜ


- በንጉሥ ሄሮድስ አግሪጳ በ 44 ዓ. ም ሰማዕት ሆኖል

የሐዋ ፲፪፥፪

ከሐዋርያት መካከል የመጀመሪያው ሰማዕት
በሐዲስ ኪዳን ሰማዕትነቱ የተፃፈለት ሐዋርያ

- **ሚያዚያ 17 ዕረፍቱ**

የሐዋርያት ሥራ 12
1፤ በዚያም ዘመን ንጉሡ ሄሮድስ መከራ
ያጸናባቸው ዘንድ ከቤተ ክርስቲያኑ
በአንዳንዶቹ ላይ እጁን ጫነባቸው።
2፤ የዮሐንስንም ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ
ገደለው።



#3

ቅዱስ ማትያስ



በአስቆሮጡ ይሁዳ ምትክ
የተሾመ ሐዋ ፩፥፳፭ ~፳፮


የሐዋርያት ሥራ 1
20፤ በመዝሙር መጽሐፍ፦ መኖሪያው ምድረ በዳ ትሁን የሚኖርባትም አይኑር፤ ደግሞም፦
ሹመቱን ሌላ ይውሰዳት፥ ተብሎ ተጽፎአልና።
21-22፤ ስለዚህ ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ ከእኛ ዘንድ እስካረገበት ቀን ድረስ፥ ጌታ ኢየሱስ በእኛ መካከል በገባበትና በወጣበት ዘመን ሁሉ ከእኛ ጋር አብረው ከነበሩት ሰዎች፥ ከእነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ይገባል።
23፤ **ኢዮስጦስም የሚሉትን በርስያን የተባለውን ዮሴፍንና ማትያስን ሁለቱን አቆሙ።**
24-25፤ ሲጸልዩም፦ የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ፥ ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ስፍራ ይሄድ ዘንድ በተዋት በዚህች አገልግሎትና ሐዋርያነት ስፍራን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው፡ አሉ።
26፤ ዕጣም ተጣጣሉላቸው፥ **ዕጣውም ለማትያስ ወደቀና ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቈጠረ።**

የቅዱስ ማትያስ ሰብከት

- "በላዕተ ሰብእ " የሚባሉ ሰዎች ወዳሉባት ሀገር ተመደበ በርባሮስ / ሩሲያ
- ደማስቆ

ፍፃሜ

- ፊላዎን በተባለች ቦታ ዐርፎል
- **በዓለ ዕረፍቱ መጋቢት 8 ቀን ይከበራል**



ዋቢ

- መፅሐፍ ቅዱስ (ሐዲስ ኪዳን)
- ገድለ ሐዋርያት
- ወንጌል አንድምታ
- የሐዋርያት ታሪክ



ወስብሐት ለእግዚአብሔር !